Ministry of justice

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፳፩ ቀን ፪ሺ፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 6
ADDIS ABABA 30th December, 2010

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፬/፪ሺ፫ ዓ.ም

ለግብርና ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ......ገጽ ፭ሺ፭፻፹፫

CONTENTS

Proclamation No. 694/2010

International Development Association Financing Agreement for Agricultural Growth Project Ratification Proclamation… Page 5683

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፬/፪ሺ፫

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለግብርና ዕድገት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፸፩ሚሊዮን፰፻ሺ ኤስ.ዲ.አር /ሰባ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፲፱ ቀን ፪ሺ፲ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፲፪ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለግብርና ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፬/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 694/2010.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS** a Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit in an amount not exceeding SDR 71,800,000 (seventy one million eight hundred thousand Special Drawing Rights) for financing Agricultural Growth Project, was signed in Addis Ababa on the 19th day of October 2010;

**WHEREAS** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Financing Agreement at its session held on the 21st day of December 2010;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for Agricultural Growth Project Ratification Proclamation No. 694/2010".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፲፱ ቀን ፪ሺ፲ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 4783-ET የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፸፩ሚሊዮን፰፻ሺ ኤስ.ዲ.አር /ሰባ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፳፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Credit Number 4783-ET signed in Addis Ababa on the 19th day of October, 2010, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of SDR 71,800,000 (seventy one million eight hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 30th day of December, 2010**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት